የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፴፫
አዲስ አበባ — መጋቢት ፴ ቀን ፲፱፻፹፱

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

3rd Year No. 33
ADDIS ABABA – 8th April, 1997

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፸/፲፱፻፹፱ ዓ.ም.
ከኩዌት መንግሥት ጋር ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋትና ዋስትና ለመስጠት የተደረገው ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ........................ ገጽ ፭፻፲

## CONTENTS

Proclamation No. 70/1997
The Investment Promotion and Protection Agreement with the State of Kuwait Ratification proclamation ........................ Page 510

### አዋጅ ቁጥር ፸/፲፱፻፹፱

### ከኩዌት መንግሥት ጋር ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋትና ዋስትና ለመስጠት የተደረገውን ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

በኩዌት መንግሥት እና በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት እና ዋስትና ለመስጠት መስከረም ፬ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ.ም ኩዌት ከተማ ላይ ስምምነት የተፈረመ ስለሆነ ፤

ስምምነቱ በሚገባ ሥራ ላይ የሚውለው በተዋዋዮቹ ሀገሮች ሕጐች መሠረት ስምምነቱ መጽደቁን የሚያረጋግጡ ሰነዶች በዲፕሎማቲክ አካላት አማካኝነት ልውውጥ ከተደረገ በኋላ እንደሚሆን በስምምነቱ ውስጥ የተገለጸ በመሆኑ ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መጋቢት ፴ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው ስለሆነ ፤

በሕገመንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት ከዚህ እንደሚከተለው ታውጇል ።

፩· <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "ከኩዌት መንግሥት ጋር ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋትና ዋስትና ለመስጠት የተደረገው ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፸/፲፱፻፹፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### PROCLAMATION NO.70/1997
### A PROCLAMATION TO RATIFY THE INVESTMENT PROMOTION AND PROTECTION AGREEMENT WITH THE STATE OF KUWAIT

WHEREAS, an Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the state of Kuwait was signed in Kuwait city on the 14th day of September, 1996;

WHEREAS, it is stipulated in the Agreement that the Agreement shall formally come into force after the exchange of notes confirming ratification in compliance with the constitutional requirements of the contracting states;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Agreement at its session held on the 8th day of April 1997;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 sub Articles (1) and (12) of the constitution, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "State of Kuwait Agreement on Investment Promotion and Protection Ratification Proclamation No.70/1997."

፪· ስምምነቱ ስለመጽደቁ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኩዌት መንግሥት መካከል ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋትና ዋስትና ለመስጠት መስከረም ፬ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ·ም ኩዌት ከተማ ላይ የተፈረመው ስምምነት ጸድቋል ፡፡

፫· የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ባለሥልጣን ኃላፊነት

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ባለሥልጣን ስምምነቱ በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል፡፡

፬· አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከመጋቢት ፴ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ·ም· ጀምሮ የጸና ይሆናል ፡፡

አዲስ አበባ መጋቢት ፴ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ·ም·

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፕሬዚዳንት

2. *Ratification of the Agreement*

The Agreement on the Promotion and Protection of investments signed in Kuwait City on the 14th day of September, 1996 between the state of Kuwait and the Federal Democratic Republic of Ethiopia is ratified.

3. *Power of the Ethiopian Investment Authority*

The Ethiopian Investment Authority is hereby empowered to implement the Agreement.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 8th day of April. 1997.

Done at Addis Ababa, this 8th day of April, 1997

NEGASO GIDADA (DR.)

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE